# Chromebook ማዘጋጀት

**Chromebooks የ Google መተግበሪያዎችን እና የድር አሳሽ የሆነውን Google Chrome ይጠቀማሉ (** ![chrome] **)፣** ስለዚህ የእርስዎን Chromebook ለመጠቀም **የ Google Gmail መለያ** ያስፈልግዎታል።

**የ Gmail መለያ ከሌለዎት፣** አንድ መለያ በሚከተለው ላይ ይፍጠሩ mail.google.com።

በመቀጠል፣ እነዚህን እርምጃዎች ይከተሉ:-

**1. Chromebook ን** በኪቦርዱ በላይኛው ቀኝ በኩል ባለው የኃይል ቁልፍ **ያብሩት:-**
**2. ከ Wifi አውታረ መረብ ጋር ይገናኙ።** የእርስዎ Chromebook ***Network not available (አውታረ መረብ ማግኘት አልተቻለም)*** ካለ፣ አውታረ መረብን ለማግኘት እና ለመገናኘት ከታች በቀኝ በኩል ያለውን ቁልፍ ይጫኑ።
**3. ወደ Chromebook ዎ ይግቡ።** ሙሉ የ Gmail አድራሻዎን እና የይለፍ ቃልዎን ያስገቡ እና ***Next (ቀጣይ)*** የሚለውን ይጫኑ። ይህንን መልእክት ያያሉ:- ***Managed by seattlecentral.edu (በ seattlecentral.edu. የሚተዳደር)***
**4. የእርስዎን የ Chromebook መለያ ያዘጋጁ። *Accept and continue (ይቀበሉ እና ይቀጥሉ)*** የሚለውን ይጫኑ።
**5. የጎግል ፕሌይ መተግበሪያዎችን እና አገልግሎቶችን ይቀበሉ። *More (ተጨማሪ)*** የሚለውን ከዚያም ***Accept (ይቀበሉ)*** የሚለውን ይጫኑ።
**6. እንዲሁም የ Google Assistant ን ለመጠቀም መምረጥ ይችላሉ። *የ Google Assistant እዚህም እንደሚሰራ ሲያዩ፣ No thanks (አይ አመሰግናለሁ)*** የሚለውን ወይም ***I agree (እስማማለሁ)*** የሚለውን ይምረጡ። የሚስማሙ ከሆነ:-

- ጉግል ረዳትን ለማስጀመር፣ "Hey Google (ሰላም ጎግል)" ይበሉ። ከዚያም መረጃውን ያንብቡ እና ***Agree (እስማማለሁ)*** ወይም ***No thanks (አይ አመሰግናለሁ)*** የሚለውን ይጫኑ።
- እርምጃዎቹን በመከተል Assistant ዎን ድምጽዎን እንዲያውቅ ያስተምሩት። ***Skip (ዝለል)*** የሚለውን ጠቅ በማድረግም እንዲሁ እዚያው ማቆም ይችላሉ።

***7. Get started (ጀምር)* የሚለውን ይጫኑ።** አሁን የእርስዎን Chromebook ለመጠቀም ዝግጁ ኖት።

## የ Chromebook ማያ ገጽ መሳሪያዎች

የሚታዩት ምልክቶች በምስል ሊለያዩ ይችላሉ።




- የመተግበሪያ አስጀማሪው በእርስዎ Chromebook ላይ ያሉትን መተግበሪያዎች ያሳይዎታል።
- ተጨማሪ መተግበሪያዎችን ለማውረድ ወደ ጎግል ፕሌይ ስቶር (Google Play Store) ይሂዱ።
- በመስመር ላይ ለመሆን Google Chrome ን ይጠቀሙ።